ከጥንት ጀምሮ ተንኰል ካህን ያሳደገው አጋሚዶ ።
ድርሰትሂ ሰፌ አዝመራዬ በማሳ ድካም ነጕዶ
ረግፎ ቀር ለሰው ሳይሆን በመኪና በሬ ተኪዶ
በወርጎ ማኅተም መከር ከሰማይ መናፈግ ወርዶ
መቶታልና ለሰው እስኪ መስለው ድረስ ባዶ
ሰብልን ለማውደም የወረደው ድኅነት የጥፋት በረዶ

## ምዕራፍ ፪ ሸዋ (አንጎል) ።

## መ ግ ለ ጫ

ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች መካከል የሚገኝ የባዕድ ግዛት የማያዋስነው ሸዋ ነው። ያሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ አዲስ አበባ የሚገኘው በዚሁ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ነው ። ሀገሩ ሜዳ ነው ፡ ረጃጅም ዛፍ ሣር ብዙ ወንዝ የለበትም ፤ በዳር በዳሩ ከመለግ የማይበልጡ ዱሮች አሉ ። በሜጫ አውራጃ መጠነኛ ጫካዎች ይገኛሉ ፡ ማን ኛቸውንም እኽል እንደ በታው ነው እንጂ ያበቅላል ። ግን አዝመራው የሚያፈራው በሰው ልፋትና ትጋት እንጂ በመሬቱ ስባት አይደለም ።

ሰው በጣም ታታሪ ነው ፡ የሚሠራውን ሁሉ የሚያደርገው በምክርና በትዕግሥት እንጂ በፍጥነት አይደለም ፡ አንጎልም የተባለበት ምክንያቱ ይህ ነው ፡ አውራጃዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ) መናገሻ ፤ ለ) ሰላሌ ፤ ሐ) ደብረ ብርሃን ፤ መ) ደብረ ሲና ፤ ሠ) ናዝሬት ረ) ጨቦና ጉራጌ ፤ ሰ) አምበ ።

<u>ወ ሰ ን</u> ፡ በሰሜን ወሎና ጎጃም በምዕራብ ፡ ወለጋና ጅማ በደቡብ ፡ አሩሲ በም ሥራቅ ሐረርጌ ናቸው ።

ዓሣ ያላቸው ወንዞች ፤

አዋሽ ፡ ጀማ ፡ ጉደር ናቸው ። ትንንሽ ሐይቆች ፍል ውኃ ፡ መዋት በብዙ ይገኝበታል ።

አንጎልሽ ሸዋ ነው ምታስቢበት
ሌት ተቀን ይሠራል ያላንዳች ዕረፍት
በጆሮሽ ሰምተሽ በዓይንሽ ያየሽውን
አውጥተሽ አውርደሽ በልብሽ ያለውን
በአንጎልሽ አስበሽ አመጣሽ አልጋውን
በአንጎልሽ የሚኖር አልጋ ምሥጢርሽ
በቃልሽ ተነግሮ ሰው ዐወቀብሽ
ዐይንሽም አየና ይህንን ምሥጢር
ላንጎል መለሰለት ከዚያው እንዲኖር

በጣም የሚገርመኝ ይህ ሥራሽ ነው
የወጣውን ምሥጢር አንጐል መለሰው

<u>ኢትዮጵያ</u> ምሥጢሬስ አይወጣም ወዴትም አይሄድ
አንጐሌ ቢበሳጭ ልቤ ቢናደድ
በድምፄ አንጐራጐርሁ እንደ መልካም ወንድ
በሁለት እጇ ይዤ ወገቤ መንግሥትን
አንጐረጉር ነበር እያሰማሁ ድምጤን
ቃሌ ሲዝገመገም እንዲያ ቈጭቶኝ
ከድምፄ በቀረ ማንም አልሰማኝ

<u>ልብ</u> መልካም አድርገሻል እናት ልንገርሽ
በአንጐልሽ አስበሽ ምሥጢር መያዝሽ
አንጐልሽ አስቦ መክሮ በሠራው
አካላትሽ ሁሉ በጣም ደስ አለው
አንጐልሽ ማሰቡ መልካም ነው እናቴ
በሚሠራው ሥራ ታደሰ ሕይወቴ

<u>ኢትዮጵያ</u> በአንጐሌ እኰራለሁ እናትህ በጣም
ሚጠቅም ተሆነ ምክር አይጠላም
ተጽፏል በዳዊት ምክር ለልባም
ታድናለች እንጂ ሰውን አትጐዳም
አወጣ አወርድና ሁሉንም አስቤ
እሠራዋለሁኝ በምክር ሰብስቤ
አስቦ ማይሠራ ሥራውን በአንጐል
እንስሳ ነውና ሰው ነኝ አይበል
ነገሥታት መሳፍንት ልጆቼ በሙሉ
በአንጐል እያሰቡ ሕዝብን ይገዛሉ
ሕዋሳቴ ሁሉ ያድራሉ በጤና
ያስተዳደር ምንጩ አንጐሌ ነውና
አንጐሌ አሰላስሎ ያሰበውን ልቤ
በያዘው መሠረት አእምሮ መዝገቤ
ሕጉ ተሰናዳ ማስተዳደሪያው
ሕጋጌው ተበጀ ሕዝብን ሚመራው
ውሳኔው ድንጋጌው ወሰን የሌለው
ብያኔው አማረ በዓለም ተደነቀ
ትእዛዝ ተከበረ መብት ተጠበቀ
ሀብታም ባለጸጋ ነጋዴና ቱጃር

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ከወንበዴ ጋራ አደሩ በፍቅር ።
ጥቁር ባርያ ብሎ ይሸጥ የነበረ
አርነት ወጣና ግፉ ሁሉ ቀረ
ነጻነት አገኘ ሆነ ፍጹም ሐራ
እኩል ተቈጠረ ከጨዋ ልጅ ጋራ
የሰው ልጅ በሙሉ ፍጹም ደስ አለው
ፍትሑን ስላገኘ ሚያስተካክለው ።
ሐራ ባሪያ ቀረ ሕጋጌያቸው ጠፋ
አንጕል እያደረ ዕውቀትን አሰፋ
ነገሥታት መሳፍንት መኳንንት በሙሉ
አንጕሌ በሠራው ይዝመነመናሉ ።

ል ብ በጣሙን ይገርማል ያንጕልሽ ሥራው
ወሬውን የሰማ ዓለም ደነቀው ።
በአንጕልሽ አስበሽ ብርድ እንዳይነካሽ
መንዝ ያረባሺውን በጉን ሸልተሽ
ሕዝቡን አለበስሺው የሠራሽውን
በርኖስና ባና የሚሞቀውን
ይፋትና ወግዳ መዝነሽ ጥጡን
በጅሩ ዲጋንሽ የነደፍሽውን
በሞረት ሸማኔ በአንኮበር ባለእጅ
አሠርተሽ ጥበብ ሸለምሽው ለልጅ
ነገሥታት ልዑላን ራስ መሳፍንት
ኀያላን መኳንንት ብዙ ሊቃውንት
ደምቀው እንዲታዩ ሁሉም አንድነት
ታለብሻቸዋለሽ ዕውቀት ካባ ላንቃ
ከራሳቸው ተርፎ ላለም የሚበቃ
አዳም ጤፍን ዘርተሽ ሁሉን በያይነቱ
ምግብ ትሰጫለሽ ለመላ ፍጥረቱ ።
ጨልያ ወርጄ ባየው ሀብትሽን
አንጕሌን ማረከው ሰለበው ልቤን
አዝመራ ለማየት እርሻ ስጕበኝ
ቀልጮ ነበረ በቈሎሽ ውጦኝ
በእጁ መሞልቀቁ መቍረጡ ቢያቅተው
መጥረቢያውን ይዞ መጣ ሊቈርጠው ።
በአዋሽ በበረሃው በናዝሬት አውራጃ

ጥጡ መሰብሰቡን መከተቱን እንጂ
በጣም ያስፈራራል ቈላው መተሐራ
ተቃጥሎ የጠፋው በእሳተ ገሞራ ።
በእሳተ ገሞራ ምንም ቢቃጠል
ፈስሶበት ይታያል ቊጥር የለሽ ኀየል ።
ሳላና ቀጭኔ የሜዳ ፍየል
ከግመሉ ጋራ ሲሮጥ ይታያል
አርጃኖና ዘንዶ አዘና ጉማሬ
በመተሐራ ሐይቅ ይታያል ከዳሪ ።
በሸዋ በዙሪያው በቈላ ቈላው
የሚታየው ቅጠል በጣም ለምለም ነው ።
እንደዚህ ለማሰብ የቻለበትን
ያንጐልሽን ምግብ ንገሪኝ ሁሉን ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ምግብማ ምን ገዶ ሳለሁ እናትህ
እነግርሃለሁኝ አንተ ከሰማህ ።
በደብረ ሲናና በግንደ በረት
ዘላለም ይዘንማል ማርና ወተት
መስሎ ሲግበሰበስ ታላላቅ ዘሆን
ያምበን ላም በየኸው ደግሞም በሬውን
የካራ ቆሬ ከብት ወጥቶ ሲሰማራ
ይመስላል በሜዳው የራዛን አሞራ
እኽልም እዘራለሁ በሰፊው ሜዳዬ
ለራበው ላቀና እንደልቦናዬ
ጅሩን ስንዴ ዘራሁ ይፋትን ማሽላ
አዳንም ነጭ ጤፍ ሰላሌን በሞላ
አሞቦ ላይ ጋግሬ ልጆቼን ላበላ
በቈላና ምስር ዐተር አደንጓሬ
አብሽ በሶ ብላ ድንብላል በርበሬ
ጠመጅና ስንዴ ብዙ ጥራጥሬ
ተቈጥሮ የማያልቅ ያበቅላል አገሬ
አዝሙድ ከሰናፍጭ ሰሊጥ በሶ ብላ
ያለማል መሬቴ ሁሉንም በሞላ
መራቤቴ ወርጂ ብበላ ማሽላ
ወዜም ተመለሰ መልኬም በጣም ቀላ ።
የጅሩን ገብስና የተጉለትን ጤፍ

ሰላሌ ወርጄ ብበላ ሳላርፍ
ወዜ አንጻባረቀ እንደ ክረምት ጐርፍ
ብርቱካን ከሜጫ ሙዝ ከደብረ ሲና
ተክዬ በላሁኝ እሱም ሆነኝ ጤና ።
ይፋትና ጅሩ ነጭ ጤፍ ያለው
ባምቦ በሰላሌ በቄላ ቄላው
ካዳ ነጭ ጤፍ ጋር ሚወዳደር ነው ።
ወይፈንና ጊደር እንስሳ በሞላ
ሲወፍር ነው ሚያድር ያምቦን ጨው ከበላ
ይህንን ከዛቀ በሬውም ያርሳል
ላዘምር እንድችል ማቀናው እኽል ።
በአንዛቡ ለቃቅሞ ሆዱን እንደ ሞላ
ቡ ይላል በሬዬ ከዛፎቹ ጥላ
ጥጋት እንደማይቀድ እንደማያርስ ሁላ
ባየኸው ሲንሻሻ በጌና ፍየሌ
በመራቤቴና በመንዝ በሰላሌ ።
በጉራጌ ምጣድ ስጋግር እንሰት
አስመስለዋለሁ እኔ ከያዝሁት
ከባሕር የመጣ ነጫጭ ወረቀት
በሀገረ ሕይወት በግንደ በረት
እሰበስባለሁ ማርና ወተት ።
ሲቀትር ቁጭ ብዬ ከዛፎቹ ጥላ ።
ጠብሼ እበላለሁ የባሕር ማሽላ ።
ጤፍና ማሽላ እኽሌን ሁል ሰብስቤ
እበላዋለሁኝ በወተት በቅቤ ።
ከዚህ ሁሉ በላይ ወተት እጠጣና
ሕይወቴ ሲስማማኝ ምግቡም ሲሆን ጤና
ጊቤ እወርዳለሁኝ ልዋኝ ውኃ ዋና
ከዚያም በተረፈ አዋሽና ዤማ
ስዋኝ እውላለሁ ክረምት ከመጣማ
ባዋሽና ጉደር በቢሽፍቱ ሐይቅ
አላለቀም ዓሣው ሁል ጊዜም ቢዛቅ

<u>ልብ</u> አንጐልሽ የጠራው ከሩቅ ሚያስበው
ለካንስ እማዬ ይህን በልቶ ነው ።
የት ነው የገዛሽው ይህንን ልብስ እመ

በጣም ያስደስታል ልቤም ተገረመ ።

ኢትዮጵያ    ልጄ እነግርሃለሁ ካልገባህ ምሥጢሩ
ጥጡን መዘንሁና ከይፋት ከጅሩ
እጀ ሥራ አግብቼ በወግ በመሥራት
እፈትለዋለሁኝ ቁጭ ብዬ ሌሊት
አንጐሌ እንዲደሰት ራሴም እንዲኰራ
አከናውናለሁ ልዩ ልዩ ሥራ

ልብ    ምግብሽ ያስደንቃል ይገርማል ሥራሽ
አንኮበር ላይ ፈትለሽ መንዝ አሠርተሽ
ንድፍ የመሰለ ጉምሽን ለብሰሽ
ጥላም ባትመኚ ፀሐይ ባያይሽ
ዋዕዩ የጠናበት ቈላው ተመኘሽ

ኢትዮጵያ    የነጭ ጥጥ ልብሴ የምታየውም
ከፀሐይ ነው እንጂ ብርድ አያድንም

ልብ    እናቴ በጣሙን እግዚአብሔር ይስጥልኝ
ልብስና ምግብሽን በሰፊው ነገርሽኝ
በንጐል ምታሰቢው ያማርኛን ቅኔ
እባክሽ ንገሪኝ እመ ልስማው እኔ

ኢትዮጵያ    ቅኔም ብቻ አይደለ ብዙ ግጥም አለኝ
በል ስማ ልንገርህ አንተ ከጠየቅሽኝ ።

ልብ    ገጣሚ መሆንሽን አልጠራጠርም
ቅኔ እንዳለሽ እንጂ ግጥም አልፈልግም ።

ኢትዮጵያ    አንጐሌ አደነቀህ ወደደህ አንተን
ለይተህ ስላወቅህ ግጥምና ቅኔን
በሌሎች ለምጄ በሞኛሞኞቹ
በቂሎች ለምጄ በገራገሮቹ
ግጥም ቅኔ ነው ብለው በከንቱ ሲተቹ
ይህንኑ ይገዤ ላንተ ብነግርህ
ስሕተት ነው ስላልሽኝ አመሰገንሁህ
እኔውም ባስበው ባሰላስለው
ቅኔዬ ነው እንጂ አቻ የሌለው
ግጥምስ በያገሩ ዘይንተረፍ ነው
አሁንም እንዳልሽው ስማኝ ልንገርህ
ኀብርና ሰም ለበስ ሁሉም አለልህ

የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጸሐፌ ትእዛዝ አለቃ ወልደ ጊዮርጊስ በየጊዜው የተናገሩት የአማርኛ ቅኔ፣ ሀገራቸው አማራ ሳይንት ነው ይባላል እኛ ግን በኖሩበት በዚሁ ጽፈ ነዋል ።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጋላን ድል አድርገው ሲመለሱ
ጋላ ታቦት ሁኖ እንደ ጊዮርጊስ
ስለቱን ጠገበው አንገቱ ድረስ

ንጉሡ በግ አርደው፣ የሚሉትን ለመስማት በሽሮ ስላበሏቸው
አንኮበር ላይ ሁኜ ቁንዲ አልታይ አለኝ
በጉም ተሸፍኖ እየተሠወረኝ

በንጉሡ አኰረፋና ቤት ልሥራ ብለው ተሰናብተው ሂደው በመቅረታቸው፣ የሚ ከተለውን ንጉሡ ስለ ላኩባቸው መልሰዋል፤

ጭቃው ሳይቦካ ሳይሠራ ቤቱ
ከማገር ተቀምጠው አለቃ ሽፈቱ
እኔ እየነገርሁህ አታድርገው ዋዛ
ለኔም አገር ስጠኝ አንተም በደንብ ግዛ
ንጉሡ ከሞቱ በኋላ
የሣህለ ሥላሴ ከሆንሁት ወዳጅ
ቤቴ ፈርሶ አልጠጣም እኖላለሁ ጠጅ
እኔ ምን ቸገረኝ ቢሰበር ዋዲያቱ
ደቂ አለ ጌታዬ የበላሁበቱ
ራሳቸው ሊሞቱ ሲጠራሞቱ
ጐንደር ወርጄ ተክኘ ልብሰ ተክህኖ ለብሼ
ታዩኛላችሁ እኔን
ነገ ገብቼ ሳኖን

አቤቶ ሰይፉ የሞተ ጊዜ አንዲት አልቃሽ ያስለቀሰችው
የሸዋ መኳንንት እንግዲህ ዕረፉ
ተመዞ የነበረ ተከተተ ሰይፉ

ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋ ከገበረ በኋላ ስለከዳቸው ተናደው እጅ እጁን ቈርጠዉት ስለሄዱ የሚከተለው ተለቀሰ
ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ
የሸዋን መኳንንት እጅ ነሥተው ሄዱ

ከደራሲው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ አድማሱ ዘሸዋ (ዜጋመል) በየጊዜው የተቈጠረ።
በከብት ማረጃ በቁራው
ደጎናውን ብልት ማይገዛው
የሚገዛው ሥጋ ለመብል

ቅንጥብጣቢ ሁኗል ።
ከሁሉ ሁሉ ከቤት ክፍል
አዳራሽ ተወዷል ።
የምንበላው ቢያምረን
ሥጋ ገዝን ሂደን
ቢያመጣልን ይኸ አምባዛ
ተሁሉም ጨው አበዛ ።
ወተት አልበው ከላሚቱ
ቅቤ ሲያወጡ ሰነበቱ
እነዚህ ሰዎች በሙሉ
አገፋፍን ያውቃሉ
ያለፈው አልፏል ለነገሩ
ተነጋግረናል በምሥጢሩ
እኛ ምነለው አሁን
የፊቱን የፊቱን ።
ድንኳናቸውን ሲጥሉ
ተራዳውንም ተከሉ
ጥሩ ሁኖ ሁሉ አማረ
ብቻ አውታራቸው ዘረ
ችግኝ በብዙ ተክለን
ታች አምና ክረምቱን
ዘንድሮ እንኳ በበጋው
ለጋብቻ ነው ።
ወይን በብዙ ተክለን
ወራቱ ደርሶ ሲያውከን
ከኛ ሁላችን ማን ተሻለ
የቈረጠ ከሌለ ።
እነዚህ ሰዎች ሠለጠኑ
ብዙውን አገር አቀኑ
ብዙ አሏቸው መኰንኖች
ፊታውራሪና ደጃዝማቾች
ይሠምር ነበር ሥራቸው
ራስ ቢኖራቸው ።
ወንድሜ ተጣልቶ ድንገት
ከአንድ ሰው ጋራ ትላንት

የተጣላንበት ምክንያት
ያችን ልጅ ጥሎበት
ድንገት አጥፍቼ ጥፋት
ስጠበቅ በእሥር ቤት
ቈይቼ ነበር እስከ ዛሬ
አሁን ግን ተፈታሁ በወሬ
ብዙ ዛፎች ተክሎች ሳሉ
ለጋ ለጋውን ንቀል አሉ
ምነው እንደዚህ የሆኑቱ
ለጋብቻ መጠላቱ ።
ወንድሜና እኔ ተማክረን
መልካም ጥገት ገዛን
የቀለቧ ነገር ከተቻለ
አጋዥ አይጠፋም አለ ።
በሽታው አይሎ ቢበዛ ሞትም
እረ ምንም ቢሆን ቀባሪ አይጠፋም ።
ያቺ ጉብል ታማ በዛሬው ዕለት
አትተርፍም እያሉ ነግረውን ድንገት
ልጠይቃት ብሄድ ከቤቴ ትላንት
እውነት ሙታ ኑሯል በቃኝ ዐወቅሁት ።
የበርኖሱ ለባሽ እያነሰ ሄደ
የአጐዛውም ለበሽ እያነሰ ሄደ
ጥቁሩንም የሚለብስ እያነሰ ሄደ
ነጭ ለባሹ በዛ ይህ ዘመን ዐበደ
ከወፎቹ ሁሉ ከኛ ሚገኙት
እነሆ የኛ ሰዎች እጅግ ሚወዱት
በጣሙን በጣሙን በጣሙን ማማት
ከዚያ ከማሚጋር ማንም እንዳይቀርብ
በዋጅም ተለፈል ተገትሯል ዘብ
ትእዛዙን አፍርሶ አዋጁን ቢያስቀር
የደረሰ ሁሉ ይቀጣል በምር ።
መሰንቆ ክራሩን እናንት አምጡልን
በገና ነው እዚህ እኛውስ ያለን ።
መልካም ልብስ ሁነዋል ሸማ ጋቢ ኩታ
ልግም በገላ ግን ቀረ ሁኖ ተርታ ።

ፍየል ብዙ ታርዶ በግም እጅግ ሞልቶ
ሥጋ ረከሰ አሉ በላተኛ ጠፍቶ ።
ግንብን እንድሠራ ብዙ ሰው ቢመክረኝ
ወንድሜ ሥጋዬ አፈርሳለሁ አለኝ
ምንኵስና ዐስቤ ቆብ አሰፍቻለሁ
ቅናትም አልሻ ቅናት ታጥቄያለሁ ።
አደሱን ተቀብታ እንሶስላ ብትሞቅ
እንኳን በግልጽና ቢሆንም በድብቅ
የሚደርስም የለ ማንንም ብትጠይቅ ።
የያዝሁት ጐራዴ ግና ጥሩ ነበር
አሽሟጣጩ በዛ የማይረባ ነገር
ከጌጣጌጥ ሁሉ ከዛሬው ከጥንቱ
መስቀልን ይወዳል አሁንስ ወጣቱ
ረብ እንደሌለ እንዳልሠራ ሁላ
ብረቴ በምን ነው እንዲህ የተጠላ ።
ድኃው ሀብት የሌለው ይዘን ይመረር
ከቶ ባለጸጋ በምን ይቸገር ።
እረ ለምን ይሆን ቄማጣ የበዛ
ስለጠፋ ነው ወይ ባለ እጅ እንደዋዛ ።
ጥሉላት ተናቁ ሥጋውም ተጠላ
ሽሮ መብላት ሁኗል የዘመኑ መላ ።
ዓመቱን በሙሉ የሥራ ቀን ሁኖ ሁሉንም ቢሠሩ
እረ እንዲህ ይቅር ወይ አንድ በዓል ማክበሩ ።
ጥሬ የሚመገብ የባቄላ ንፍሮ
እንደምን ይቀራል መብላቱ ጠርጥሮ ።
በዚህ መሬታችሁ ዝናሙ ካየለ ውሃውም ከበዛ
እረግረግ መሆኑ አይቀር እንደዋዛ ።
ወለባውን ውሰድ ወስፌውንም ጣል
የነሱማ ሥራ በመዋጥ ሁናል ።

## ስለ አርምሞ ።

ወደ ዓለም ብመጣ እንዲያው በድንገት
ጐራዴ ምላስን ሚሆን ረዳት
ሰጡኝ ዘመዶቼ ብለው ሥራበት

በአፍ አፎት ከትቼ እኔም አኖርሁት
የሚሠራበት ቀን እስኪ መጣለት
ቃል ስለቱ ወጦ እንዳያስቸግር
ውላጋ ከንፈርን አበጀሁ በምር ።
በዚህ ስለቴ ባርድ ሽኽር ድርሰትን
ጮማ ቋንቋን ፈርቶ ዘዬ ብርንዶን
አስበርግጎት ነበር የቀመሰውን
ይኸንንም ትቼ ሂስ ሪማን ባርድ
አብዱል ብለው ሄዱ አርገውት አመድ ።
የጉራጌው ጌታ በጣም ተቈጣና
ገዛና በሰፊው ርስትን ትሕትና
ዐርፎ ተቀመጠ እንዲኖር በጤና ።
ከብዙ ወቅት ወዲያ ከብዙ ዘመን
ቀሳጢ መጣና በግድ ውላጋን
ለመሳብ ሞከረ ስለት ሊፈትን ።
ቅቤ ወሬን ይዞ ሊያሽ ውላጋውን
ቢያቅተውም ጊዜ በኀይል በጉልበት
ሌላ መላ መታ አመጣ ብልሐት
ቀሳጢውን ይዞት የወሬን ዳፍንት
ያመጣውም ቅቤ እንበለ ምሕረት
ተጠጥቶ ቀረ ሆነበት ቍጭት ።

## ስለ ቅኔ ።

በአፍሪቃ ምሥራቅ በኢትዮጵያ
ለሚኖረው ንጉሥ ለሌለው አምሳያ
ሰላምታ አቀርባለሁ እጅግ በትሕትና
በጣሙን ለሚሰይ ለቅኔአችን ጀግና ።
የዚህ ንጉሥ ግዛት በጣሙን የሰፋ
ዝናው የገነነ ባለወርቅ ደገፋ ፤
እስቲ ስማኝ ጉበዝ ዝናውን ላውራህ
ምጥቀት ርቀቱ ሰማይ ነው ብልህ
እንደ ምድር ሰፊ እንደ ባሕር ጥልቅ
ጆሮ ዳባ አትበል አዳምጠኝ በጥብቅ ።

የመልኩን ደም ግባት ግርማ ሞገሱን
ለሰሚታም ሆነ ወይ ለሚያይ በውን
አእምሮ አስበርግጎ ማራኪ ልብን ።
ሽማግሌም ሁኖ ጉብልን ቢመስል
በሴማ ሲያመጣው ሥራውን በውል
ካሁኑ ደጅ ጥና ሳትል ቢል ዘቢል ።
ነገርን ከሥሩ ውኃንም ከጥሩ እንደተባለው ባማራ ተረት
በውል ከልብ ሁነህ አዳምጠኝ በውነት ።
በቤተ ክርስቲያን ወይ በአዳባባይ
ጳጳሱ ሊቅ መጥቶ ለሁሉ ሲታይ
በሥነ ጽሑፍ ኪን በዚያ በውብ ሥራ
ቅኔ ንጉሥ ሂዶ ቁጭ ብሎ ሲያበራ
ጳጳሱ አቀዳጅቶ ሰምና ወርቅ ዘውድ
በትረ መንግሥት ኀብርን ይሰጠዋል በዐውድ ።
ቀጻላው ምርምር ካበ ላንቃው ዝምድ
ፍላጻ ኩታውም የማይገኝ በውድ
ቅጽል ተምሳሌ መርገፍን አጊጦ
ዓለምን ሲያስደምም ያምራል ተቀምጦ ።

## ለክረምት ።

ንጉሠ ልምላሜ ዝናም የገበሬ መኩሪያ
ታቀዳጃለህ ሁሉን ልምላሜ ጌራን በእውነት
ይሆናልና ሐሤት በዘውድ በዓልህ ክረምት
እጅግ ቀዋሚ ነውና ግብርህ ውበት
ፍጥረትም ሲያስተውልህ
ተደሞ ቀረ ሁሉም ባነገሠህ አምላክ ብልሐት
ፈረስሂ ደመናከ ተጭኖ ሲመጣ ድንገት
ይደሰታል ዓለም ሁሉ ስታመጣለት ምሕረት
ተጠቅሟልና ፍጡር በመልካም ሥራህ ከጥንት
በሠራህለት ዐውቀህ ጠልከ መልካም ሥሬት

## ለመምህሩ ።

ዓለማየሁ ሞገስ ጠቢብ የሥነ ጽሑፍ ገበሬ
በዘራህ ጊዜ ዘርን መልከም አማርኛ ለሣህል
ቀና ልቡና መሬት ፍሬውን ሊሰጥ በኃይል

ጀምሯል ዳር እስከ ዳር ብትዘራው በፍጹም ጥንቃቄ እን
ዳይሆን በልል
ስንዴ ቅኔንም ስታበራይ
ዐይታው ብቻ ጠገበ ገና ሳይቀምሰው በውል
ብርዕከሂ ማረሻከ በቃለ ፀሐይ ሲግል
ደካማ አረምን ድርሰት በገለዶ ሄስ ስትነቅል
አሸበረቀ በየተራው ዘርከ ወሰው ሰብል ።

## ለአባቱ ።

አድማሱ እሳት የሰነፍ ቅቤ ማቅለጫ
ታቃጥላለህ ተግተህ ጠንክሮ ሥራን ሙጋድ
እስኪቀልጥ ድረስ ሁሉም፣ ቅብአተ ሊቃውንት አቅድ
ለሰው ስለሚበጀው መርሐከ መንደድ
በትጋትም ስትደክም
ቄርቀዛ ቀረ ሀኬት የስንፍና ልጅ በግድ
እንቅልፍነሂ ጨማ ሥጋን ብትታየው ጊዜ ሳትነድ
ጤሰና ጠፋ ከፊታችን ፀሐይ እንዳየው በረድ
ወንተረጅነት ረመጥህ የህላዌህ ሁሉ ዝናድ
አደረገው አሬዎና ዘውግ ስንፍናን አመድ ።

## ጦቢያው ።

መልካም እንቴን ጦቢያው
በጣሙን ቀጥዋት ይኸው
እረ ምን ጥፋት አጠፋች
የአባቷን ምክር በሰማች
ያለማወቅ ጅራፍ ይዘው
ቃሏን ሰውነት ገርፈው ።
ታማ ወድቃለች በጠና
ያላገባቡ ሁና ።
አጠፋች ብለው ሰዎች ሁላ
ሊፈርዱባት ነው በመላ ።
ፍርድን ልበሱ ተነሡ
በቊርጥ ፈረዷት እነሱ
መልኳ ጠፋብኝ ወዙ

የሁኔታዋ ግዕዙ
የጥንት ውበቷ ኰበለለ
ለዛዋም ጠነዘለ
ዘዬዋንም የደም ግባት
እረ መጠጠው ማድያት ጥፋት
እረ እንዴት ያዝን አባቷ
መልኳ ጠፍቶበት ደም ግባቷ ።
መቸም ከመቃብር አይመጣ
እርሙን እንኳ እንዲያወጣ ።
እንቴ ጦቢያው ጥበብ
እስቲ ልንገረሽ ከልብ
በስቅለት ጊዜ ከዋክብት
ረግፈው ነበር በውነት
በሐኬት ምስማር ቸንክረው
በመኪና መስቀል ሰቅለው
ብዙ መከራ ማብዛቱ
ባልተወለደ አንጀቱ ።
እንደ ፀጋማይ ሁላ
ተላገዱብሽ በመላ ።
በተርታ ሁነው በየረድፉ
ቃሎችሽ ከዋክብት ረገፉ

ርእሰ ዐውደ ዓመት ዕንቍጣጣሽ
አንቺ አንቀጸ መልካም መድረክሽ ያማረ
መቃን ከጕበንሽ እጅግ የከበረ
በዓላት ክፍሎችሽ በውስጥሽ ያሉቱ
በወግ ተሠርተዋል ውብ ሁነው በስልቱ ።
በጽጌ ተጋንሽ አደይ በወግ በቅላ
መዓዛዋን ሁላ ናኝታለች ለተድላ ።
አየሩ ተመልቶ በመልካሙ ሽታ
ንቦች አዕዋፍም ሁነው በለዘብታ
ለክፍሎችሽ ውበት ለባጥ ለወለሉ
በሐዋዝ ዜማቸው ዜማን እያደሉ ።
የፈጣሪን ጥበብ የጥበብ ምሥጢር
ጠልቀው ያሳያሉ ለሁሉ ፍጡር ።
በረከት አጥልቀሽ ጸጋ ተከናንበሽ

የበዓላት አለቃ አንቺ እንቍጣጣሽ ነሽ ።
ሽለቆው ተራራው ሜዳና ገደሉ
እሊህ ያንቺ ልጆች ያሉ በየሁሉ ።
መልካም ልብስ ልምላሜን ሁሉን ሸልመሽ
ጥሩ ወተት ውኃን በወጉ ግተሽ
ፍጡር አደነቀ ቢያይ ቢመለከት
ይህች ናት እያለ ዳግማዊት ገነት ።
ርእሰ ዐውደዓመት አንቺ የተባልሽቱ
የእውነትም በላይ ነሽ ሲጀመር ከጥንቱ ።
በመባቻ ውለሽ ባመት መጀመሪያ
ሰጠሽው ላለሙ የሁሉንም መምሪያ
የሐሴት ነጋሪት የፍሥሐ እንቢልታ
ይሰማል በሩቁ ከአንደበትሽ ዋልታ ።
እንደ ሚባለውም በተረት በምልኪ
ማነኛውም ነገር ወሰው ዝባዝንኪ
ነግሦ የዋለ እንደሁ በወሩ መባቻ
ወራቱ እስኪያበቃ የሐሴት ደስታ ያደርጋል ዘመቻ ።
በዚሁ ፈር ስንሄድ በተለምነው ትልም
ያምራል አዝመራችን ይሆናል መልካም ።
ስንከፍተው በርሽን ሠረገላውን
መሎጊያውን መያዝ በደንብ አለብን
አውታር የሚያነቃ አንጕል የሚያድስ
ሕሊና ሚያረካ ገላ ሚፈውስ
ልዕልና ያለው መዓዛሽ መልካሙ
ያሰያል ሁሉንም ይናኛል ላለሙ ።
ከመስከረም ባልሽ የወለድሻት ልጅ
ሁሉንም ይዛለች አድርጋ እጅ ከፍንጅ ።
በጥቅምት አዳራሽ በኅዳር እልፍኝ
ሙሽራ አድርገሻት ሁሉን ስታገኝ ።
ይደብቅ ጀመረ ዓለሙ በብዙ
ለኔ ለኔ እያለ ሁሉም እንደ ግዕዙ ።
ከራስ ጠጕሯ አንሥቶ እስከ እግሮቿ ጥፍር
አምራ ለሽ ብላ እንደ ገደል ማር
ጥንግ ድርብ ልምላሜን ሽክ አድርጋ ለብሳ
ጉብ አለች እማኻል አበባ ነስንሳ ።

እሷን ሲያስተውሏት እያስተነተኑ
ምንኛ ረቂቅ ነው የፈጣሪ ኪኑ ።
ፈጣሪ ጊዜውን ፍጡርን ሲሠራ
በሆድ ስናሰላው በአንጐል ስናብራራ
ብዙውን የፈጀው ሥራዬ ሆይ ብሎ
በዚህች በቄንጆ ነው ሌሎቹን አቃሎ ።
ጽጌ ጽጌ ብለን ስሟን ብንጠራው
ልባችን አርግዶ በዝቷል ትርግብታው ።
እንዴያው እንደ ገብርኤል መጋቤ ሐዲስ
ድንግልን ሲያበሥራት በኃይለ መንፈስ
ብርሃን ባለም ሞላ ዓለም ሊታደስ ።
ዐሥራ አንዱን ወራት መስከረም ቢያበሥር
ልምላሜ ብርሃንን የትእምርተ ፍቅር
ይኸው አስገኘልን በሐዲስ ቀመር ።
ልባችን ሲገተት በግሩም ናፍቆት
ስናሰላ ባጅተን ከርመናል ክረምት ።
ጊዜው ረዝሞብን የዘመን ጕዳና
መፍጀቱ ተስኖን መቃኛው ጠፋና
በጣም ባክነን ነበር ዜናሽን ልንሰማ
እንኳን መጣሽልን የሰላም ዓላማ ።
በጣም የቸኰልነ ለማየት አንቺን
ለመጓዝ ነበረ በዕጣ ክፍላችን ።
የአንጐልሽ ነጻነት ያሳብሽ ጥራቱ
በኒያ ወንጌላውያን ይታያል ባራቱ
የቀን የሳምንቱ የወሩ ያመቱ
በረድፍ በረድፍ ሁኖ ስልቱና ውጤቱ ።
አንቺ በቀመርሽው ባመታዊ አቅጅሽ
በወግ ይሠራሉ የሚበጅልሽ ።
የምድር ቤትሽ ልደት በጣም ያማረው
ፋሲካ ነው አሉ እሳት ከላው ።
ከዚያም መጨረሻው የበላይ ቤት
እጅግ ከፍ ያለው ነው ሰቀሰቅ ስቅለት ።
የክፍሎችሽ ብዛት በሕንፃሽ ያሉቱ
ወሰን ምንም የለው ሲታይ በየለቱ ።
ሙገሳ ብናወርድ ለልጆችሽ ሁላ

ቅኔውን ብንዘርፈው ብንሸልል ሽለላ
በቀረርቶም ሆነ ወይ በያሬድ ዜማ
ሁሉን አቀናብረን አድርገን በሴማ
ምንም አንፈጀውም የተውኔቱን ዜና
እናብቃው ሁሉንም በአንክሮት ቃና ።
የሰውን መፈጠር ታስታውሻለሽ
ልብን ወደ አምላኩ ታቀኚዋለሽ ።
ሀብተ ምልጃ ላንቺ ከጥንት ከተሰጠ
ሁሉም ይማልድሽ እጅግ በበለጠ።
እንደዚህ ባጅተሽ ደግሞም ክረሚና
ብቅ በዩ አጊጠሽ የሰውነት ጤና ።

## እ ር ጅ ና ።

እርጅና ምሽቱ ሲጓዝ ሲያቈለቍል
አየር ሰውነትም ሲቀዘቅዝ በውል ።
መሬት ዓጽማችንም ቀስ በቀስ እያለ
ጨለማ ድካምን በወግ መልበስ አለ ።
አዬ አቶ እርጅናያ ምሕረተ ቢስ
በዘመናት ታዝሎ ሲቋፍ ቀስ በቀስ
ድንገት ይደርስና ሳያይ ሳያስብ
ሰውን ይይዘዋል በዚህ ዓለም ድብ ።
ማምለጡም ዘበት ነው የልጆች ጨዋታ
በከንቱ መደለቅ እክፉ ድጥ ቦታ ።
በዘመናት መስኮች ጅር ድንኳኑን ጥሎ
ይመጣል ሊመገብ የሰው ሥጋ አብስሎ ።
አቶ መጃጃትን በቀኙ አስተኝቶ
ባረጋዊ ገላው በወግ አስጠግቶ
ያቅበጠብጠዋል ያመል ቀልብ ነሥቶ ።
አቶ ቍርጥማትን አቶ ራስ ፍልጠትን ከአቶ ድካም ጋራ
እንዲሁም ሌሎቹን እንደ አሽን የበዙ በወግ እየጠራ
በተዋረድ አርጎ በመር በየተራ
ይመግባቸዋል ያን ሥጋ ሳይራራ
መፍነሽነሽ ጀመረ ማንንም ሳይፈራ ።
አቶ መጃጃትን በሾመው ዓመት
የዐመል ደረመን ይበዛል ድንገት

አቶ መጃጃትም ዐመሉ የከፋ ከንጨት የጠመመ
ብዙ ብዙ ይላል ምንም ያልታረመ ።
ፀሐዩን በእንቅብ ውኃውን በወንፊት እያደረጋችሁ
እሳቱንም በጭድ ባንድ ፊት ይዛችሁ
ሲበርደኝም ፀሐይ ወይንም እሳት
ሲጠማኝም ውኃ ቀን ሆነ ሌሊት
አቅርቡ በመሩ ለእግረ ሕሊናዬ ይሁነኝ ዕረፍት ።
ሲጃጃ በጣሙን ከዚያማ በኋላ
ቅደዱልኝ ይላል ያለምንም መላ
የሚተኛበቱን ያን ጠገጉን አልጋ
እስኪ አስተውሉት ይኸንን አማጋ ።
በአፍአ በውስጥ ግብሩን እየሠራ
አጥንትን አድቆ መቅኒን እየዘራ ።
አውታሮችን ይዞ እያዞረ ናላ
ያደክማል ሰውነት ደል ብሎ እያጕላላ ።
መለያልይ ሁላ ቅባታቸው አልቆ
እንደ ተጣለ አልጋ ሸንኰሩ ወላልቆ ።
ለባዊት ነባቢት ሕያዊት ነፍስ ግን
በእርጅና አሸክላ በሌት ሆነ በቀን
አትያዝም ከቶ እረ ምንም ቢሆን ።
መገረፉን ስታይ በእርጅና አለንጋ
ወደ ፈጣሪዋ በአንቃድዎ ሁና
ትማልደዋለች በህላዌው አምና ።
እባክህ ላክልኝ ገላጋይ ዕረፍት
ጕብሌ ተጠቃ ከአለንጋው ብዛት ።
ወዲያው ይመጣና ገላጋዩ ጌታ
ይገላግለዋል ጕብሉን ባንድ አፍታ ።

## እሮሮ ።

በበሽታ ዳኛ በችግር ቍራኛ
ተይዤ የነበርሁ እኔ በደለኛ
ኑዛዜዬን ስሙ ሳፈስላችሁ
ይሠራላችኋል ለእንግዲህ ወዲሁ ።
የኔም አባት ሲሞት ከዚህ አስቀድሞ
የምናዘዘውን እዚህ ለናንት ደግሞ

ተናዘልኝ ነበር በወጉ ፈጽም ።
ሀብቴም ረጀቴም ጥሪቴም በመላ
ስቈጥረው አዳምጡ በወጉ ሳሰላ
ሰምቼው የነበር ካባቴ ከቃሉ
ለናንተ ላሰማችሁ በተርታ በሙሉ ።
ኑሮዬ ኑሮዬ ኑሮዬ ባቄላ
በጊዜ ምጣድ ላይ ልበላት ብቈላ
ሳትበላ ቀረች በእሳት ሀብት በለላ ።
እረ እናንተ ሆዬ ችግር አርግዠለሁ መከራ ልወልድ
እንድገላገለው በውድም በግድ
ማርያም ማርያም በሉ ዘመድና ባዕድ ።
ኑሮዬ ኑሮዬ ኑሮዬ ባቄላ
በጊዜ ምጣድ ላይ ልበላት ብቈላ
ሳትበላ ቀረች በእሳት ሀብት በስላ ።
እስቲ ልንገራችሁ ላውጋችሁ በውነት
ዕድለ ስንኩሉ የችግር ጅረት
ፈረሰኛ ውኃ ድኅነት ኀይለኛ
ጨፈረብኝ በውል ሁኜ ዝቅተኛ ።
በኑሮዬ መልካ ሲያናጥር ዐየሁት
ያንን ጒስቊልና አጐናፍር ያሉት ።
የአዟሪት ውኃ ይኸ መበሳጨት
ገምሶት ቀረ መቸም ቃሊሜን ሰውነት ።
ኑሮዬ ኑሮዬ ኑሮዬ በቈላ
በጊዜ ምጣድ ላይ ልበላት ብቈላ
ሳትበላ ቀረች በእሳት ሀብት በስላ ።
በዚህ ዓለም ባሕር ውስጥ ስኖርበት እኔ
ተይዤ ነበረ በብዙ ጭካኔ
መከራው የበዛ አካሌ መርከብ
ሲዋዥቅ ነበረ በሐሳብ ወጀብ
ኃዘኑ ማዕበል የወጥር ይዞት
ባሕረ ሽሽ ስቃይ በውል አማቶት
ወዲያ ወዲህ ይላል ሁሉም ጠፍቶበት
እስከዚህ ደረሰ በቀን በሌሊት ።
ኑሮዬ ኑሮዬ ኑሮዬ ባቄላ
በጊዜ ምጣድ ላይ ልበላት ብቈላ

ሳትበላ ቀረች በእሳት ሀብት በስላ ።
ይኸንን መርከቤን የሚያቆም በጥብቅ
በጣሙን ዛገብኝ ሕሊና መልሕቅ ።
በዚሁ መካከል መርከቤ ተጕላላ
ሊጠፋ ነው ደቆ ሁሉም እንደሞላ ።
ኑሮዬ ኑሮዬ ኑሮዬ ባቄላ
በጊዜ ምጣድ ላይ ልበላት ብቈላ
ሳትበላ ቀረች በእሳት ሀብት በስላ ።
ሥቃይ መብረቅ መጦ ሰማይ ልቤን ቢያርስ
ተናደ መሰለኝ እንዲያው በገሚስ
ብራቅ ሁኖ መጥቶ ተልከ እንደ ማት
አንጐሌን ተራራ መታው በቀጽበት
አንጋዳ ውስጥ ጣለው ገላዬን መሬት ።
ኑሮዬ ኑሮዬ ኑሮዬ ባቄላ
በጊዜ ምጣድ ላይ ልበላት ብቈላ
ሳትበላ ቀረች በእሳት ሀብት በስላ ።

## ጾም ።

ብትነሣ ጊዜ ጾም የመንጠር እሳት
በረኸኛው መናኝ በቀጠል አጠፋት
ከጠመኑ ብዛት መናኝ ብረኸኛው ተዳከሟል በሙሉ
ቅጠል ሣር መሰለ የደከመ አካሉ ።
እሳቷ ብትጠፋ ከዚያ ከመንጠር
ከተማውን ገባች ልታጋይ አገር ።
ጐበዛዝት ሣሮች ስታገኝ ጊዜ
ማጋየት ጀመረች አበዛች አባዜ
በጥሉላት ውኆች ሣሮቹ ለምልመው
የእሳቱ ወላፈን ገረፍ ሲያደርጋቸው
አመዳቸው ወጣ ጠፉ እስከ ሥራቸው ።
እሳቷን ለማጥፋት ሲሹ መድኃኒት
ከመ ቅጽበት መጣ ደረሰ ድንገት
ሸፍንፍን ዘበኛው ያደጋው እሳት ።
ሲያጠጣቸው ጊዜ ጥሉላትን ውኆች
መለምለም ጀመሩ ሣሮቹ ጐበዞች ።
ለምልመው ካበቁ ካደጉ በኋላ

ለመክሰስ አሰቡ አረጉ መሐላ።
ጾም እቴዋን ወስደው በሃይማኖት ዳኛ
ኃጢአቷን ተንትነው ብለው ዐመፀኛ
ዳኛውም ፈረደ እንደዚህ በማለት
ዓለ መጾም ይሁን አትጣሉ በውነት
፩) ወንድና ሴቱ በድምር
በዚህ ከተማ ሲኖር
ተረዳ ዕውቀትን መርምሮ
ምሥጢር መተርጐም ዘርዝሮ
መጣፍ መግለጥን ዐወቀ
ትርጓሜንም ጠነቀቀ
ሰው ሲጠይቀው ትርጉም
ፈቶ ያስረዳል ፍጹም
ሌላውን ሥራ ትቶ
ፍችን አጥብቋል በርትቶ።
፪) ከጠቅላላው ፊደል ከፊደሉ ዘር
ሁሉንም ለይቼ አንድ ባንድ በምር
ግና ምን ይሆናል ባስበው ባሰላ
ቀን አጥቼ ቀረሁ አጥቼለት መላ።
፫) ላሞች አልወለዱ ገና ነው ሰዓቱ
ወተት ወተት ይላል ሰው ሁላ በከንቱ።
፬) ሽክሊትን ጫኑለት ለዚህኛው ወገኔ
ጀጐልን ጫኑለት ለዚያኛው ወገኔ
መቸም አፈርማ አይለይም ከኔ።
፭) ገንበውን ሳሌውን ሁሉን በያይነቱ ስሄድ አሠርቼ
በሩቅ ዐየኋቸው እሊያን ዘመዶቼ
ዕቃዎቹን ዐዩ እነርሱም ቀርበው
አገሬን ላይሰዱኝ በወጉ መክረው
አትርሳ አትዘንጋ እንዳትጥለው
ሁሉም ገል አፈር ነው የሚሰበረው።
፮) እመቤት ነጻነት እጅግ አምራልን
አልበ ሁኗል ጌጧ በአሁኑ ዘመን።
፯) ከነበቅሎ ዕቃቸው እያሉ በቅሎቹ
ምነው ፈረስ ፈረስ የሚሉ ሰዎቹ።
፰) የርሷን ነገር ተወው ተእንግዲህ አትመጣ

እውነት አምና ቀረች የልጆቿን ጣጣ ።
፱) ኃዘንተኛው ብዙ ከልብ ያዘነው
እናንተ ባሳችሁ እረ ምንድር ነው ።
፲) አበላሽቶባቸው ልብሳቸውን ሁሉ
እነሱ ስለዚህ ብል መች ይወዳሉ ።

ከደራሲው ደቀ መዝሙር አንዱ ከበደ ካሣ በየጊዜው የቈጠረው ።

ቤት ሥራልኝ ብዬው
በገንዘብ ተዋውዬው
ላየው ብሄድ ደኅና መስሎኝ
ችግሬ ቤት ሠራብኝ
አሁን በኛ ጊዜ እንጫወት እኛ
ጋላውም ጋልኛ አማራ አማርኛ ።
ቀጠሮ ማክበር ይገባናል
ብንሄድ ይሻለናል
ኑባር ይጠብቀናል ።
እራሴን አንገቴን ሲሉ ሰማኋቸው
ለምን ይዋሻሉ ሕመሙ ታፋቸው።
አታክልት አጸድቃለሁ
ብዬ እየተመኘሁ ።
ያለ ውኃስ አልተሳካም
ቦይ ቢሠራልኝ አልጠላም ።
ትምህርታችን ሁሉ ቀረ በጨዋታ
ሌላም ነገር አልል ማጥናት እዚያ ቦታ
እሸት መብላት ቢያምረው
ይዞ ዐየና ሰውዬው
ሌባ እሸቱን ቀማው
እሸት እሸት ብዬ አምሮኝ ልሞት ነው
ውብሸት ካልመጣ ይህን አልገዛው ።
ተማሪዎች ሁነን
በተማሪ ቤት ያለን
ይበዛል ቁጥራችን
እውነት የሚማሩት
ያንሳሉ በብዛት ።
ይህን አይቻለሁ ቀምሻለሁ ከዚያም

ይኸኛው ያኛውን አይበልጠውም በጣም ።
ሽፍታ ቀማኛ ቢነጥቃችሁ
ዝምታን አስለምዳችሁ
ሲመጣ ዋናው ላመሉ
ጠቅሎ ሊወስድ በሙሉ
እረ ሞትን ዝም አትበሉ
ሁለት ሰዎች ናቸው የሚለምኑህ
ለሁለት ሰው አይበቃም አንተ እንዲሁ ያለህ
ለዚህኛው ብትሰጥ ቅርቤ ነው ብለህ
ታዲያ ምን ያደርጋል ለዛ ከነሣህ ።
ብዙ ሁነን ተቀምጠን
ዕቃ ጠፋኝ አሁን
ወዲያ ወዲህ ብል አጣሁት
ሰውን በላው መሬት ።
እንስሳ ዓለም ብታውቅ ምን እንደሆነች
የሚሠሯትንም ከላይም ከታች
እንደምን አድርጋ በፍራት በሞተች ።
ከምዕራብ የመጣ ዝናም ሥልጣኔ
ቡቃያ ወገኔን ጠቅሞታል እስከኔ
አእምሮ ማሳችን ይህን በማጣት
ሳይበቅል ቈየ ብዙ ዘመናት ።
የሚጣፍጥ ነገር ኖሯል ሊቀርብህ
ብልጥ በመሆንህ መላስህ ጠቀመህ ።
በበርሜል ይጠመቅ ጠላው እንደምንም
ሲሉ ሰምቻለሁ በጋን አይጠቅመንም ።
በወንጌል ጌታ ሲናገር
እውነት እውነት ነበር ።
ከጥንት ሲነገር እንደሰማነው
ዘመድ ከዘመዱ እንደሚባለው
መኰንን መኰንን ፍለጋ ነጐደ
ድኃ ድኃውማ ቀረ ተዋረደ ።
ከሶ ጠጥቼ ደክሞኝ
መጥቶ ቢጠይቀኝ ።
እውነቱን ነገርሁት
አሻረኝ ብዬ አልሁት ።

እንደሚመስለኝ ትሄዳለህ
ምናልባት እንኳ ቢጠይቁህ
ያልሁህን ንገራቸው
አዳነው በላቸው

ለሱ ሚሆን ዕቃ አኑረን ነበረ
ሌላ ይወስደዋል እንዲያውም ካደረ
እኛ ምንቸገረን ደምበኛ ከቀረ ።
መድኀኒት ቀመስሁ ብሎኛል
ግን ያሻረው ይመስለኛል ።
ዋነኛው ጐንደሬ ምንጩ ከዚህ በላይ
የሚያስደነግጥህ የሚገርምህ ስታይ
ምንድር ነው ጩኸቱ እረግ አትልምወይ ።
በደንብ አሳምሬ በሠራሁላቸውሁ
ምነው ባታውኩኝ አሰፋ እያላችሁ ።
ቀማኛው መብዛቱ በገራችን ላይ
በቀን አያስኬድም የመሸ እንደሁ ነይ ።
እኔን ብቻ ምነው ትጠይቀኛለህ
እርሷም ተምራለች ፈትናት ከፈለግህ
የነህ ሰው ጥያቄ እንዴት ቢቀል ነው
አንድም ሰው አላለ ከበደ ክፉ ነው ።
ትናንት ከፍተህ ሂደህ ብዙ ዕቃ ጠፋብኝ
ሁለተኛ እቤቴ እንዳትመጣብኝ
ብለው ሲናገሩት አንዱን ሰማሁኝ
በማግሥቱም ሳየው ምን ሊሆን ነው ብዬ
ከፍቶት ሲገባ ዐየሁ ዛሬም ያ ሰውዬ ።

ልፈልገው ነበር እዚያ የሄድሁት
ብገባ ብወጣ ክፍሌን አጣሁት ።
የጠጁን ብርጭቆ መግዛት ይሻልሃል
የጠላ በርክቶ ኋላ ያከስርሃል ።

ከሱ መዋዋሉ ምነው በቀረብኝ
ዓለምአለሁ ብሎ እንዲያው አታለለኝ ።
አንት ጐበዝ ተሸከም አንድ ጆንያ አተር
እኔ እሰጥሃለሁ ሽልንግም ሆነ ብር
ከበደ ቀለለ ብለህ አትናገር

ትወተውታለች አግባት እያለች
ልጅቷ ለራሷ ባያት ሞኝ ነች ።
እያወቅኸው አንተ ወትሮ እንዳመመኝ
ወንድሜ አመድ መሰልህ ምነው ባትለኝ ።
ወዝ ቅባትንማ ዋ መች አጣሁኝ
አገርሽቶ እንጂ ነው ነጭ ያለበሰኝ ።
ሁሌ ምንመጣበት አይደል ቤታችን
ብለህ ባትጨነቅ አለምናምን
አትክልቴ ደረቀ ውኃ እያነሰው
መልካም ሥራ ነበር ያን በይ ብንመልሰው
ና ባክህ ወዳጅ አንተ ቀይሰው ።

## ኅብር ፡
## ልዩነት ።

እንደ ምድር አሸዋ ከመጠን በላይ ነው
የሰው እንደ መልኩ ዐመሉ ብዙ ነው ።
አንዱ ይህን ሲሻ አንዱ ያንን ይላል
ላይኛው ሲሠራ ከታች ያፈርሰዋል ።
ልጅን ወዳ ሌላው ላሟን ሲጠላ ዐየሁ
እኔስ ይህን አሳብ አልቃጣም በተውሁ
ሁለቱም ጠቃሚ እንደሆኑ አምናለሁ ።
ላሚቱ በመውለድ እንድትጠቀመን ስናይ
ሕይወትስ የሚገኝ በበሬ አይደለም ወይ ።

## የጨዋታ ሜዳ ።

በትምህርት ቤት ዕውቀት የኳሰ ሜዳ
ዐየኋት ልጆችን ስትጠቅም ሳትጐዳ
አንደኛው ሲወድቅ አንደኛው ሲነሣ
ዕውቀት ኳስም ስትሮጥ ወዲያ ወዲህ ደርሣ ።
የሚወዳትንም ሁሌ ሳታግዝ
ያገባት ሲደሰት ያጣት ሲተክዝ
እሷ ግድ የላትም አይላትም ቅዝ
ሕፃን አንጐል ያሻል ሊቈጠር ከጀግና
ከሐሳብ ጨዋታ ዐርፎ አያውቅምና
ይህንን ሲጨርስ ወደ ሌላ አቀና

ብሎም ተናገረ በዐሳብ ጕዳና ።
አንድም ቃል አለውጥ አሳቡ የሱ ነው
ይኸው አሠፍራለሁ እንደ ተናገረው ።
ዓለም ሜዳን ቁሜ እመለከታለሁ
ፍጡር የእሳት እራት ሲጫወት ዐያለሁ
ጨዋታው መጫኛ በጣም ረዥም
አንደኛው ይተካል አንዱ ሲደክም ።
የካርታ ጨዋታ ይመሰላል በምር
አንዱ ውልቁን ሲቀር አንደኛው ሲከብር
ነገር ግን ጨዋታው ያው ነው ይመስላል
አንደኛው ሲደሰት አንዱ ያለቅሳል
ተጫዋችም ተብሎ ድርሻ አለው ለሁሉም
መጫወት አለበት ቢወድም ባይወድም ።
አንዳፍታ አሸብሽቦ ሲሄድ ወደ ማታ
ሕይወት አይደለም ወይ እንዲህ ያል ጨዋታ ።
ያም ቢሆን ያም ቢሆን ሐሳብ የሌለሽ
እረ ሰንቱን ሰንቱን ታጫውቻለሽ
የጨዋታ ሜዳ ዓለም እንዴት ነሽ »

<u>ል ብ</u> ባንጕልሽ ያለውን ቅኔ ነገርሽኝ
ደግሞ ከፍከራሽ በጥቂቱ አውሪኝ

<u>ኢትዮጵያ</u> ፍከራዬንማ አንተን ካሰኘህ
እነግርሃለሁኝ አድምጥ ዝም ብለህ ።
እምቢኝ እምቢኝ ሰለባው ገማኝ
እሰቲ አንዳንድ ጊዜ ስጠው ለለማኝ ።
አሻፈረኝ ካንተም እልኛ
ፈራሁ ደመኛ
ከዚህም ብሎ ደግሞም ከዚያም
አጠራቃሚ እንደ ቅመም ።
እንዳንተ ያለ ጕበዝ እንዳንት ያለ ልጅ
ጋሻም አይገዛ ይቀማል እንጅ ።
እንዳሳሩ እንደመከራው
አልከሳም ገላው
እልኩን ቢያዩ እንደ ጋሬጣ
ጦር የወጣለት እንደፈንጣጣ ።

ልቡ ያሰበውን አፉ ማይመልሰው
እልኩ እንደሽዋ የሚቸረፈሰው
ጦር እንደገለባ የሚያግበሰብሰው
ከኋላ ነው ሲሉት ከፊት የሚደርሰው ።
እንዲህ ወደ ማታ ሊለው ድንግርግር
የጦሩ ባላባት የጐራዴው ነብር ።
ጣሊያን ቢገጥም ከዳና ሙግት
እግቡ አገባው በሠራው ጥይት ።
አሁን ማን አለ በዚህ ዓለም
ጣሊያን አስደንጋጭ ቀን ሲጨልም ።
ግብሩ ሰፊ ነው ጠጁ ባሕር
የዳኘው ጌታ ያበሻ አድባር ።
ሽዋ ነው ሲሉት ዐድዋ የታየው
ሽናሽ መላሽ ወንዱ አባ ዳኘው
ወዳጁ ሳቀ ጠላቱም ከሳ
ተንቀሳቀሰ ዳኘው ተነሳ ።
ፈረሱ ዳኘው ሚሰቱ ጣይቱ
ምጥዋ ወርዳ ቀዳች ወጥ ቤቱ ።
ልክ እንዲገባ ያጐበጐበው
የዳኘው ቀኝ እጅ በል አንተ ቃኘው ።
ሄደ ዘለቀ እስከ ጠረፉ
የቃኘው ፈረስ ያሞራ ክንፉ ።
ልቤ ለዘለዓለም የማይለየው
የዳኘው አሽከር መኰንን ቃኘው ።

ል፡ብ ጥያቄን ሁሉ ስለተቀበልሽ
እመ ፍቀጅልኝ መወድስ ልስጥሽ ።
ኦ አንጐል የሸዋ አማካሪ
ትዘግበዋለህ ሁሉን በምድረ ሸዋ ጽሕፈት ቤትህ
ማንኛቸውንም ዓለም እንደ ባሕሪው ችለህ
ፍርድን እስክትሰጠው ድረስ አይናገርም አፍህ
እንዳልሰማህም እየሰማህ
ትታገሣለህ ሁሉን በልብህ ሰሌዳ ጽፈህ
ደግሞምሂ በወጣ ጊዜ ማስተዳደሪያው ሕግህ
ይታዘዙታል በትሕትና መሳፍንት ሕዋሳትህ
ይቀበላልና ለሰርክ ሥርወ መንግሥት ኃይልህ
የሚወጣውን ትእዛዝ ከንጉሠ ነገሥት የዳም ሥርህ ።